# የሁለት ትውልዶች ወግ

## ከቤይሩት እስከ አውሮፓ

ክፍል ሦስት

ከበልጅግ አሊ

ዐረቦች ብቻ አይደሉም በኛ በኢትዮጵያውያን ላይ ጨካኞቹ እርስ በራሳችንም እንጨካከናለን ። አንተን ያሰቃዩህ እኮ አበሾች ናቸው ። እኔ ፈረንሳይ ውስጥ አንድ አበሻ ቤት ተቀጥሬ ነበር ። ሙሉቀን ምግብ ሠርቼ ፣ ልጅ ጠብቄ ፣ አስቤዛ ገዝቼ ፣ አልጋ አንጥፌ ሁሉንም አድርጌ 350 ኤሮ ነበር የማገኘው ። ሰዎቹ ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ነው የሚሰሩት ግን እንደ ገረድ ነበር የሚያዩኝ ።በዛ ሃገር 350 ኢሮ በቀን 2 ሰዓት በሳምንት አምስት ቀን ተሰርቶ የሚገኝ ነው ።እኔ የፈቃድ ወረቀት ስለሌለኝ ብቻ ነው ይህንን የምሰራው ። ደግሞ ቋንቋ ስለማልችል አበሻ ቤት ይሻላል ብዬ ነው ።አንዳንዴ ሴትየዋ ኢትዮጵያ ውስጥ 350 ኢሮ ማለት ስንት ነው ? ብላ ትጠይቀኛለች። ብዙ ነው የምከፍልሽ ብላ ትመፃደቃለች ። እሷ በእኔ ችግር እንደምታተርፍ እየረሳችው ። ይገርመኝና ሴትየዋ ጤፍ የምሸምተው አዲስ አበባ ይመስላት ይሆንን ብዬ አስባለሁ ። እኔም እንደሷ አውሮፓ መኖሬን ትረሳዋለች ።

የቤት ሠራተኛነት የጀመርኩት ቤይሩት ውስጥ ነው። ቤይሩት በጣም ውብ ከተማ ሆና ከሌሎች የዐረብ ከተማዎች ስትወዳደር ነፃነት ያለባት ናት።በእምነትና በአለባበስ የጎላ ችግር አይታይም ። ሕዝቡም የሠለጠነ ነው። በሃገሪቱ ውስጥ ብዙ የውጭ ዜጎች ይኖራሉ። ቤይሩት ውስጥ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን አብዛኛዎቹ ሴቶች ናቸው ። የወንዶች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው ።

በዐረብ ሃገር በእኛ ላይ የሚደርሰውን ስቃይ ባለፈው ትንሽ ጠቅሼልህ ነበር ። ይህ ደግሞ ከተቀጠርንበት ቤት ቤት ይለያያል። በተለያ አክራሪ እስላሞች ቤት የተቀጠረች ኢትዮጵያዊ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋታል ። በእነዚህ አክራሪ እስላሞች ቤት ሥራው ቀንና ሌሊት ነው ። አንዲት ትንሽ ጥፋት ቅጣቱ በአሰቃቂ ሁኔታ መደብደብ ብቻ ነው ።ለምሳሌ በማንኛውም ጊዜና ሰዓት ስትጠራ በአፋጣኝ መምጣት አለባት ። ትንሽ ብትዘገይ ጥፊና እርግጫ ይከተላታል። ለዕእረፍትና ለመኝታ የተመደበ ሰዓት የለም። ቀጣሪዎችዋ በፈለጉ ጊዜ ልትታዘዝ ትችላለች። ጥፋቱ ደግሞ ከፍተኛ ከሆነ ለምሳሌ ሸሚዝ ብታቃጥል፣ ተልካ ሄዳ ብታረፍድ ፣ በተለይ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ወይም የሌላ ሃገር ዜጎች ጋር ስታወራ ከተደረሰባት የሚደርስባትን ሥቃይ መገመት ይከብዳል።

የስራ ኮንትራታችን ሦስት ዓመት ነው ። ይህንን ሦስት አመት መቻል ይኖርብናል ። ሕይወትህን አቆይተህ ወደ ሃገርህ ለመመለስ ከፈለግህ ይህንን ሦስት አመት መታገስ ነው አለበለዛ ግን በየቀኑ በጥፊና በርግጫ መደብደብ ነው ። በየአረብ ሃገሩ ስንት ሴት እህቶቻችን ወገባቸው ተሰብሮ የመሥራቱም ሆነ የመኖሩም ዕድል የጨለመባቸው ብዙ እንደሆኑ እንዳሉ እመነኝ ።

ግን እኛን ኢትዮጵያውያንን ምን እንደነካን አላውቅም ። ትላንት እዚህ እኛ ጋ አንድ ልጅ እራሱን ሰቀለ። እሺ እሱ ምን ሆኖ ነው ትላለህ ? እዚህ አውሮፓ ውስጥ ነው ፣ ሥራ አለው ፣ ችግር የለበትም ፣ ሥራስ ባይኖረው የሚበላው የሚጠጣው የሚኖርበት የሚለብሰው አያጣም ፣ ቤተሰብ መርዳት ይችላል ። ምን ሆኖ ነው እራሱን የሚገድለው ። ግን በዐረብ አገር ባርነቱ ሲበዛብን ከፎቅ ወርደን ለመፈጥፈት ያልሞከርን የለንም ። ሞት ከዚህ ባርነት ይጣፍጣል ብለው ያሰቡትም እራሳቸውን አጥፍተዋል ።

EthioLion.com

ከሁሉ የሚከብደው ለብዙ ጊዜ ከሰው ጋር ሳትወያይ ብቻህን መቀመጥ ነው ። ዐረቦቹ በከፍተኛ ደረጃ የሚከለክሉት ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘትን ነው ። መንገዱን አጥንተህ ትጠፋለህ ብለው ሰለሚያስቡ ነው።ግን በድብቅ ጥረት ማድረግ በጣም ያስፈልጋል ። ሃሳብህን የምታካፍለው ፣ የምታወራው ሰው መፈለግ አለብህ ። እንዳንተው በጎረቤት የተቀጠሩ ሌሎችን መፈለግ ይኖርብሃል ። ችግርህን ስትወያይ ይቀልሃል ። ለብቻህ ከማውጣት ከማውረድ ይሻላል። ሰውነትን ዘና ያደርግና ችግርህ የቀለለ ይመስልሃል ። ግን ተመልሶ ያው ነው ።

እኔን የገጠሙኝ ሰዎች በጣም ክፉዎች ነበሩ ለማለት አልደፍርም ።የእስልምናን ሃይማኖት በትክክል የሚያውቁ ናቸው ። በጣም አስቸጋሪዎች አልነበሩም ። በሳምንት አንድ ቀን ዕረፍት ሰጥተውኝ ነበር ። በእዛ ቀን ቤተከርስትያንም ሆነ የፈለግሁበት መሄድ ይፈቀድልኛል ። ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው ሰለ አውሮፓ መስማት የጀመርኩት ። የተሻለ ኑሮና ጥሩ ኑሮ እንደሚገኝ አወቅሁ ።ምንም ጥሩ ሥራ ቢኖረኝም ለመሄድ ወሰንኩ ።ቤይሩትን የለቀቅሁት ከአምስት ዓመት በኋላ ነው።

አራት ሆነን ነበር የተነሳነው ሦስት ኢትዮጵያዊ ሴቶችና አንድ የሲሪላንካ ወንድ ልጅ።ግን እሱ  ምን ወንድ ይባላል!  ከእኛ በላይ ነው  እየተንሰቀሰቀ የሚያለቅሰው ! ።ጉዟችን ወደ ቱርክ ከተማ ካንታኪያ ነው ።ከሊባኖስ ስንነሳ  ከቀኑ አስረ አንድ ሰዓት ነበር ። ሁለት ሰዓት በመኪና ከተጓዝን በኋላ ወደ ሶርያ ድንበር ደረስን።ድንበሩን መሻገር የምንችለው በእግር ሰለሆነ በጨለማ ጉዟችንን ጀመርን፡፡አርባ አምስት ደቂቃ ከተጓዝን በኋላ ከአንድ ወንዝ ደረስን ። የወንዙ ጥልቀት እሰከ ደረታችን ይደርስ ነበር ። ለመሻገር የወሰደብን ጊዜ ከፍርሃቱ ጋር ሰላሳ ደቂቃ ነው ። ከዛም በፍጥነት በእግር መጓዝ ነበርብን ። ሁለት ሰዓት እንደ ተጓዝን የሶሪያን ድንበር ጥሰን ገባን ። ሶርያ ጫካ ውስጥ ሌላ አንድ ልጅ ተጨመረ ።

ጋሼ የጨለማ ጉዞ ምን ይመስልሃል ? ከባድ ነው መደናበር ነው ። የምትረግጠው ጉድጓድ ሊሆን ይችላል ፣ የሚወጋ እንጨት ወይም ብረት ይኖራል ። ደግሞ መፍጠን ያስፈልጋል መደበቂያው ቦታ ሳትደርስ ከነጋብህ መያዝህ ነው ። ብሩህ ሆኖ የሚታይህን የአውሮፓ ኑሮ እያሰብክ ፣ ሰው ከደረሰበት  እደርሳለሁ ብለህ እየተመኘህ መጓዝ ነው ። በየመሃሉ ደግሞ የአምስት ደቂቃ እረፍት ይሰጥሃል ።የሶሪያን ግዛት ለመጨረስ  ሌሊትና አንድ ቀን መጓዝ ይጠይቃል። በበነጋታው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ቱርክ ድንበር መድረስ አለብን ። ካልሆነ ግን የሚጠብቀን  ሰው ላይኖር ይችላል ። እኔ ሁለት ጊዜ አደጋ ስለደረሰብኝና ከሚመራን ሰው ጋር ገንዘብ ጨምሩልኝ በሚል አለመግባባት ስለተፈጠረ ዘግይተን ከምሽቱ አራት ሰዓት ደረስን ። የደረሰብኝ አደጋ በመጀመሪያ አንድ ትልቅ መንገድ ለመሻገር አጥር ስንዘል ብረት እግሬን መታኝና አቆሰለኝ ። በሌላ ጊዜ እንደዚሁ ብረት ሆዴን ወጋኝ ። ይህ ሁሉ በቀን ቢሆን ላይደርስ ይችል ነበር ።በሌሎቹም ላይ እንደዚሁ አደጋ ደርሶባቸዋል ።

በመዘግየታችን ምክንያት የሚቀጥለው ጉዞ ተሰረዘና አንድ ወንዝ አጠገብ እንድናድር ተዘጋጀ ። በጣም ደክሞን ስለነበር ተኛን ። ቁስሌ እየባሰብኝ መጣ።ሌሊቱን በሕመም ስቃይ በማሳለፌ የሚመራን ሰውዬ አዝኖልኝ ወደ ገጠር ሄዶ መድሃኒት አመጣልኝ። ወንዙ  ጋ ተደብቀን አምስት ቀን አደርን ። ሌሎች ተጨምረው 20 ሆንን ። ከነርሱም ውስጥ አበሾች ሦስት ብቻ ነበርን ። ሌሎቹ ከተለያዩ ሃገር የመጡ ናቸው። በስድስተኛው ቀን ከምሽቱ 2 ሰዓት ጉዞ ጀመርንና በበነጋታው አንድ ሰዓት ላይ ካንታኒካ ደረስን ። ሁላችንም እንደገና ተበታተንን ። በተለያዩ ሰዎች ቤት ውስጥ ተመደብን ። ከዛ በአውቶብስ 50 ዶላር ከፍለን ወደ ኢስታንቡል ጉዞ ቀጠልን ። ከአስራ ስድስት ሰዓት ጉዞ በኋላ ኢስታንቡል ገባን ።

ኢስታንቡል ላይ ሌላ መንገድ አዋቂ ማፈላለግ ነበረብን ። በጀልባ  ወይም በእግር ለማቋረጥ ወደምትሄድበት ሃገር የሚወሰነው  እዚህ ነው ። መጀመሪያ ዓላማዬ ወደ ጣልያን ለመጓዝ ነበር ግን ሰላልተሳካልኝ ጉዞዬን ወደ ቡልጋሪያ ጀመርኩ ። ሌሎቹ አብረውኝ የነበሩት ሴቶች ገንዘብ ከዘመድ እንደተላከላቸው ቀድመው ሄዱ ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ከኔ ጋር ሁለት አበሾችና 27 የሌላ ሃገር ዜጎች ሆነን ተነሳን ።

Ethiolion.com

ስድስት ሰዓት ከተጓዝን በኋላ ቱርክ ቡልጌሪያ ድንበር ደረስን። የቱርክ ድንበር የሚጠበቀው በውሻ ነው ። ውሻው ካገኘህ እስክምትሞት ድረስ ቢነክስህም የቱርክ ፖሊሶች አያስቆሙልህም ። ይህ በጣም አደገኛና የተለመደ አጋጣሚ ነው ። እኛን የወሰደን ግለሰብ ግን በደንብ ሁኔታውን አጥንቶ ሰለነበር ይህ አጋጣሚ አልደረሰብንም ። ዋናው ያስቸገረን የፓውዛ መብራቱ ነው ። መብራቱ ወደኛ በሚበራበት ጊዜ መደበቅ አለብን ። ድንበሩ በሽቦ የታጠረ ስለነበር መሬቱን እየቆፈርን ድንበሩን ተሻግረን ጉዞ ቀጠልን ። ከብዙ ስቃይና መከራ በኋላ ድንበሩን ተሻገርን ። አሁን ሳስረዳህ ይቀላል ። አንዳንዴ እዛው መሞትን ትመርጣለህ ። በውሾች የተነከሱትን ሰዎች ታሪክ ለሰማ ሰው ቡልጌሪያ ክልል እስከምትገባ ሰውነትህ በእያንዳንዱ ኮሽታ ይሳቀቃል ።

ሲነጋ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ መኪና ጠበቀንና  ወደ ሶፊያ ቡልጋሪያ ዋና ከተማ ይዞን ሄደ ። ከዛም ወደ ግሪክ ለመጓዝ ጥረት ጀመርኩ ። ሁለት ጊዜ አልተሳካልኝም ተመለስኩ ። በሦስተኛው ግን ተያዝኩ ።

በሶፍያ እስር ቤት ለሁለት ወር ቆየሁ ። እስር ቤቱ በጣም አስቀያሚ ነው ። ቢሆንም ለሴቶች በጣም ይሻላል ። ወንዶቹን ግን የቡልጌሪያ ፖሊሶች በጣም ይደበድቧቸዋል ። ምግቡ የተቀቀለ የሻገተ ድንች ብቻ ነው ። ውሃውም የሚሸት ነው ። ከሁለት ወር በኋላ ተፈታሁና ሳልሞክር አምስት ወር በችግር ቡልጌሪያ ውስጥ ኖርኩ።

ከዛ ጉዞ ወደ ግሪክ አደረግሁ ። ጉዞው ከባድ ነው ። ስድስት ተራራ መውጣትና መውረድ አለብህ ። ታራራ ስልህ ደግሞ ትንሽ እንዳይመስስልህ ። ድንጋይ ብቻ የሆነ ቀጥ ብሎ የቆመ ተራራ ነው ። አንዳንዴ  ላይ ደርሶ ተንሸራቶ መውረድ አለ ። በመንፏቀቅ እጃችን ሁሉ ቆሰለ ። ሦስት ሱሪ ለብሰን እሱን አልፎ ሰውነታችንን ይጎዳናል ። ከአራት ቀን መከራ  በኋላ ተሰሎንቄ ግሪክ  ገባን ። አንተ ደርግ አሰቃይቶ ጠባሳ እግርህ ላይ እንደተወልህ  አሳይተኸናል ።የግሪክ ተራሮች እኛም ሰውነት ላይ ጠባሳ ትተው አልፈዋል ። የተንፏቀቅንበት ቂጣችን ጠባሳው አለ ።

ከተሰሎንቄ ወደ መጨረሻው ግሪክ በባቡር ነው የሄድኩት ። የማልመው አውሮፓ ደረስኩ ። እዚህ እንደመጣሁ ሌላ ችገር ገጠመን። ለካ ያ እንደዛ የጓጓንለት አውሮፓ ሌላ የራሱ ችግር አለው . . . . . . . . .

በሌላ ቀን ሁሉንም ቤቴ ጠራኋቸው ። ዛሬ የጠራኋችሁ አንድ ቁም ነገር ላወያያችሁ ነው ።ብዙ ጊዜ ኢሕአወሊ ስል ትሰሙኛላችሁ። ኢሕአወሊ ምንድነው ብላችሁ ጠይቃችሁኛል። ኢሕአወሊ በኢሕአፓ ውስጥ የወጣቶች ክንፍ ነበር ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዩታዊ  ወጣቶች ሊግ ማለት ነው ። የሊጉ አባላት ሕዝባዊ መንግስት ለመመስረት ፣ የዴሞክራሲ መብቶች አለገደብ እንዲሰጥ እንታገል ነበር ።በሠራተኛውና በገበሬው ላይ የሚደርሰውን ጭቆናን እዲቆምም እንጠይቅ ነበር ። የሃገራችን የወደፊት ዕድል በጣም ያሳስበን ነበር። በዛ ወቅት በኢሕአወሊ ያልታቀፈ ወጣት ይኖራል ብዬ አላስብም ።ሁላችንም ለሃገር መሞትን እንደክብር ነበር የምንቆጥረው ። በዛ ጊዜ እነዛ ለሃገር የሚያስቡ ወጣቶች በቀይ ሽብር ተገደሉ ።ተስፋችን ጨለመ ። ሃገ

የኢሕአወሊ ዓላማ ቢፈፀም ኖሮ ይህ ሁሉ በእናንተና በመሰል ወጣቶች ላይ የሚደርሰው  መከራ ላይደርስ ይችል ነበር  ብዬ አምናለሁ ።  . . . . . . . . . . .

ተፈፀመ

ይህንን ፅሁፍ በሚመለከት ሀሳብ መስጠት ለምትፈልጉ በዚህ ኢሜል አድራሻ ተጠቀሙ።
beljig.ali@gmail.com